


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## በእውነተኛ ፍቅር ስንሞላ፥ ስለ ሌሎች ማሰብ እንጀምራለን



## በቃል የሚጠና፦ ያዕቆብ 2፥26

*“እኔ ስለ ሁላችሁም እንደዚህ ማሰብ ይገባኛል፤ ምክንያቱም በሙሉ ልብ ስለምወዳችሁ ነው፤ ስለ እናንተ እንደዚህ የማስብበት ሌላው ምክንያት ደግሞ የምሥራቹን ቃል መሠረት ለማስያዝ መከላከያዬን በማቀርብበት ጊዜና አሁንም በእስራት ላይ ሳለሁ እናንተ ከእኔ ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ስለሆናችሁ ነው።”*
*(ፊልጵስዩስ 1፥7)*

### 1 ጳውሎስ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ከልብ ይወዳቸው ነበር

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ ምዕመናንን *“ስለ ሁላችሁም እንዲህ ማሰብ ይገባኛል”* ይላቸዋል። ይህን ያለበትን ሁለት ምክንያት ይሰጣቸዋል። አንደኛው፥ *“በሙሉ ልብ ስለምወዳችሁ ነው”* ይላቸዋል። በአገራችን “ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው” የሚል ትክክል ያልሆነ አባባል አለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን “እውነተኛ ፍቅር” ሲኖረን፥ በዚያ ሰው ላይ ያለን እምነት እንደሚጨምር ይነግረናል። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *“በሙሉ ልብ ስለምወዳችሁ፥ በእናንተ ላይ ትምክህት አለኝ”* ሲላቸው፥ ይህንን እውነት ማረጋገጡ ነው። ጳውሎስ ለቆሮንቶስ አማኞች በጻፈው ደብዳቤ ላይ የፍቅርን ባሕሪ ሲገልጽ፥ *“ፍቅር በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል፤ ፍቅር በሁሉም ላይ ተስፋ ያደርጋል፤ ፍቅር በሁሉ ነገር ይጸናል”* ይላል (1ኛ ቆሮ. 13፥7)። ስለዚህ *“ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው”* የሚለው የአገራችን አባባል፥ ከላይ ያየነውን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚቃረን እናያለን። እንደ እግዚአብሔር ቃል በእውነተኛ ፍቅር ያፈቀርነውን ሰው እናምነዋለን፤ በእርሱም ላይ ተስፋ እና ደርጋለን። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ አማኞች ላይ የነበረው የፍቅሩ ጥልቀት በእነርሱ ላይ የነበረውን እምነት፥ ወይንም ተስፋ ማድረግ የበለጠ ጨመረለት። ለምናገለግለው ሕዝብ ፍቅር ሳይኖረን ማገልገል እንችላለን። ይሁን እንጂ፥ አገልግሎታችን ፍሬ የሌለው ከመሆኑም በላይ፥ በአገልግሎታችን ምክንያት በሚደርስብን ግጭትና አንዳንድ አለመግባባት ምክንያት ቶሎ ተስፋ ቆርጠን አገልግሎታችንን ትተን ለመውጣት ይቃጣናል። እውነተኛ የነፍሳት ፍቅር ካለን ግን፥ ስለምናገለግላቸው ነፍሳት ሕይወት ስንል ብቻ፥ የሚደርስብንን መከራና ችግር መታገስ እንችላለን። ያለእውነተኛ ፍቅር ንጹህ የሆነ አገልግሎት መስጠት አይቻልም። ልቡ በፍቅር የተሞላ ሰው፥ ፍሬ ያለው እውነተኛ አገልጋይ ይሆናል። ጳውሎስን በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንደኛውና ትልቁ፥ የሚያገለግውን ሕዝብ በጣም ይወድ ስለነበረ ነው።

### 2 ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን ስለሚወዳቸው በጣም ያስብላቸውም ነበር

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *“ስለ ሁላችሁም እንዲህ ማሰብ ይገባኛል”* ያለበት ሁለተኛው ምክንያት፥ የመከራውና የስደቱ ተካፋዮች በመሆናቸው እንደሆነ ይናገራል። *“ወንጌልን በምሰብክበት ጊዜም ሆነ አሁንም በእስራት ላይ ባለሁበት ጊዜ ከእኔ ስላልተለያችሁኝ ነው”* ይላቸዋል። የሚያስደንቀው ጳውሎስ ወህኒ ቤት በተጣለበት ወቅት፥ እርሱ በመታሠሩ ምክንያት የእግዚአብሔር ቃል ያልታሠረ መሆኑ ነው። ጳውሎስ በአገልግሎቱ ብዙ ፍሬ ያየበት ጊዜ፥ ስሙ፥ ወይንም ዝናው ከምንጊዜውም የበለጠ የገነነበት ዘመን ቢኖር፥ እስር ቤት በነበረበት ወቅት ነው። በሰንሰለት ታስሮ በሮማ ወታደሮች በሚጠበቅበት ወቅት እንኳን፥ ሊያዩት ለሚመጡት ሁሉ ወንጌልን በድፍረት ይሰብክላቸው ነበር። ይጠብቁት የነበሩት የሮማ ወታደሮች እንኳን ሳይቀሩ በጳውሎስ ስብከት ይነኩ ነበር። የእስራት ዘመኑ ፍሬያማ እንዲሆን፥ በሚደርስበት መከራ ሁሉ ተስፋ እንዳይቆርጥ ምክንያት የሆኑት የፊልጵስዩስ አማኞች፥ በታሰረበት ወቅት ከአጠገቡ ሳይለዩ፥ በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ በመርዳት እስከ መጨረሻው ድረስ የመከራው ተካፋዮች በመሆናቸው ነው። የፊልጵስዩስ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል በሕይወታቸው የሚለማመዱ፥ ወይንም ቃሉን በተግባር የሚያውሉ መሆናቸውን እናያለን። ዕብ. 13፥2-3 ላይ *“...ከእነርሱ ጋር አብራችሁ እንደ ታሰራችሁ ያህል ሆናችሁ እስረኞችን አስታውሱ፤ እናንተም እንደ እነርሱ መከራ የምትቀበሉ ያህል ሆናችሁ መከራ የሚቀበሉትን አስቡ”* ይላል። ይህንን ትዕዛዝ፥ ጳውሎስ በታሠረበት ወቅት የፊልጵስዩስ አማኞች በተግባር ላይ አውለውት እንደነበር ጳውሎስ በጻፈላቸው ደብዳቤ ላይ ጠቅሶታል። እኔና እናንተ የጌታን ሥራ ለመሥራት በምንታገልበት ወቅት፥ የጳውሎስን ዓይነት እስራትም እንኳን ባይሆን፥ አንዳንድ ያልጠበቅናቸው ክፉ ሁኔታዎች እንደማያጋጥሙን፥ በቀጥታም ሆነ በተዘ

ዋዋሪ በሚደርስብን ስደት ምክንያት ነፍሳችን የምትጨነቅበት ወቅት ሊኖር ይችላል። በእንዲህ ዓይነቱ መጥፎ ሁኔታ ውስጥ ስናልፍ፥ አንዳንዶቻችን ተስፋ በመቁረጥ የያዝነውን ጥለን፥ ከአገልግሎታችን ሸሽተን ለመውጣት የሚቃጣን ጊዜ ሊኖር እንደሚችል ግልጽ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ከጎናችን የሚቆሙ፥ የሚያጽናኑን፥ ሸክማችንን አብረውን የሚሸከሙ፥ ሌላው ቢቀር ብሶታችንን ስንናገር የሚያዳምጡ ሰዎችን ማግኘት ምን ያህል ትልቅ ድጋፍ እንደሆነ በዚህ ልምምድ ውስጥ ያለፍን ሰዎች እናውቃለን። የጳውሎስ አገልግሎት ትልቅና ሰፊ ነበር። የፊልጵስዩስ ምዕመናን አገልግሎት ግን በሰው ዘንድ ሲታይ የጳውሎስን ያህል ትልቅ ባይመስልም፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ እንደሆነ፥ በዚያው መጠን ጌታም በመጨረሻው ቀን ሽልማታቸውን እንደሚሰጣቸው እርግጠኞች ነን።

## 3 ከዚህ ክፍል ውስጥ የምናገኘው ጠቃሚ ትምህርት

### ሀ *ፍቅር በሁሉም ላይ እምነቱን ይጥላል*

የፍቅር ባህሪ አንደኛው፥ የምናፈቅረውን ሰው "ማመን" እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የምናገለግላቸውን ሰዎች "መውደድ" ብቻ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ለአሁንም ሆነ ለወደፊት፥ ለክብሩ የሚሆን የአገልግሎት ስጦታ በውስጣቸው እንዳኖረ ማመንና መቀበል ይገባናል። ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞች በእምነታቸው ገና ጀማሪዎች ናቸው በማለት ሳይንቅ፥ ወደፊት መሆን የሚችሉትን በእምነት ዓይን በማየት ስለ እነርሱ በተደጋጋሚ እግዚአብሔርን ሲያመሰግን በጻፈላቸው መልዕክት ውስጥ እናነባለን።

### ለ *ትንሽም ቢመስለን አገልግሎታችንን አንናቅ*

አገልግሎታችን ምንም ያህል ትንሽና በሰው ዓይን ጎልቶ የማይታይ ቢመስለንም፥ በሚያጋጥመን የአገልግሎት ዕድል ሁሉ ተጠቅመን የሚገባንን ካደረግን፥ በጌታ ፊት አንድ ቀን ሽልማት እንደሚያሰጠን አንጠራጠር። የምንሰጠውን አገልግሎት ትንሽነቱን አይተን፥ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት መስጠታችን አይሰማን እንጂ፥ በጎ ለተደረገለት፥ ወይንም አገልግሎት ለሰጠነው ሰው ትልቅ ነገር ሊሆን እንደሚችል አንዘንጋ። ትንሽም ቢሆን ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች በአስፈላጊው ጊዜ ደርሰን የእርዳታ እጆቻችንን ከዘረጋን፥ በመጨረሻው ቀን ከእግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ፥ "ያለምንም ፍሬ፥ ባዶ እጄን መጣሁ" ብለን አናፍርም።


***የሕይወት ምስክርነት፦—*** አንድ ጊዜ ሆላንድ አገር፥ በአንድ መንደር ውስጥ ለብቻው የሚኖር *ሀንስ በርጀን* የተባለ አንድ ሰው ነበረ። ብዙ የሚታይ ሀብትና ንብረት አልነበረውም። ትዳር መሥርቶ ልጆች አልወለደም። መልኩ በጣም አስቀያሚ ስለነበረ የመንደሩ ልጆች የቅጽል ስም አውጥተውለት በአጠገባቸው ባለፈ ቁጥር ይቀልዱበትና ይስቁበት ነበር። ከመንደሩ ውስጥ ጥሩ ሰላምታ የሚሰጠው አንድም ሰው አልነበረም። ከልጆቹ መካከል ግን *አን ማርቲን* የተባለች ልጅ፥ እንደተቀሩት ልጆች በመቀለድ ፈንታ ሁልጊዜ ፈገግታ ታሳየው ነበር። ያ ሰው አንድ ቀን ድንገት ታመመና ሞተ። የመንደሩ ሕዝብ ሊቀብሩት ሲያዘጋጁት፥ የኑዛዜ ቃሉን ያሰፈረበትን ወረቀት አገኙ። ኑዛዜውም "በየቀኑ ወደ ቤቴ ስገባና ስወጣ፥ የመንደሩ ልጆች፥ በሙሉ ተሰብስባችሁ ትቀልዱብኝና ታፌዙብኝ ነበር። በሕይወቴ ዘመን ሙሉ *ከአን ማርቲን* በስተቀር የፈገግታ ፊት ያሳየኝ ሰው የለም። ስለዚህ እስከ ዛሬ ድረስ ያጠራቀምኩት 40 ሺ ብር ለአን ማርቲን እንዲሰጥልኝ ተናዝዣለሁ" የሚል ነበር። አን ማርቲን ለዚያ ሰው ምንም ትልቅ ነገር አላደረገችም። ያደረገችው ነገር ቢኖር ለዚያ ሰው የፈገግታ ፊት ማሳየት ብቻ ነው። ይሁን እንጂ፥ ትንሹ በጎ ድርጊቷ ያልጠበቀችውን በረከት እንዳስገኘላት እናያለን።

### ሐ *ስለሌሎች መከራና ችግር ስናስብ፥ ጌታ ለእኛ ያስብልናል*

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *"እኔ ስለ ሁላችሁም እንደ ዚህ ማሰብ ይገባኛል"* ያለበት ምክንያት በችግሩ ጊዜ፥ በእሥራቱ ዘመን ከጎኑ ስላልተለዩት ውለታቸው ተሰምቶት እንደሆነ ተመልክተናል። *"...የምሥራቹን ቃል መሠረት ለማስያዝ መከላከያዬን በማቀርብበት ጊዜና አሁንም በእስራት ላይ ሳለሁ እናንተ ከእኔ ጋር የእግዚአብሔር ጸጋ ተካፋዮች ስለሆናችሁ ነው"* ይላቸዋል። የሌሎችን መከራና ችግር በልቡ የሚሰውር ሰው፥ ምንጊዜም ቢሆን ብድራቱን ከጌታ እንደሚቀበል የታወቀ ነው። ልቡ በፍቅር የተሞላ ሰው፥ የሚያደርገው ተግባር ለሰው ዓይን ጎልቶ የሚታይ ባይሆን እንኳን፥ የአገልግሎቱ ፍሬ በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ነው። በልቡ ውስጥ ለሌሎች ሥፍራን የሚሰጥ፥ በሕይወቱ ራስ ወዳድነትን ያሸነፈ፥ ከራሱ ፍቅር የተላቀቀ ሰው ነው። የፊልጵስዩስ አማኞች መንፈሳዊ ሕይወት ከላይ የገለጽነውን ይመስላል።

---

የመዳንንም ራስ ቁር



**የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።**

**(ኤፌሶን 6፥17)**




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን ስለ እናንተ ማሰብ ይገባኛል ያለበት ሁለት ምክንያት፥

   (ሀ)

   (ለ)

2. ጳውሎስ ስለ ፍቅር ባህሪ ሲገልጽ ምን አለ? (1 ቆሮ. 13፥7)

3. የምናገለግለውን ሕዝብ ሳናፈቅር ብናገለግለው ውጤታችን ምን ዓይነት ይሆናል?

4. በአገልግሎታችን ውስጥ አንዳንድ ችግር ሲያጋጥ መን ታግሰን ማለፍ የሚያስችለን ምንድነው?

5. ጳውሎስ በአገልግሎቱ ብዙ ፍሬ ያየበት ጊዜ መቼ ነው?

6. ጳውሎስ እስረኞችን ስለመጠየቅ፥ በመከራ ውስጥ ስለሚያልፉት ምን አለ? (ዕብ. 13፥2-3)

7. በልቡ ውስጥ ለሌሎች ሥፍራን የሚሰጥ ሰው እንዴት ያለ ሰው ነው?

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...


1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስን አማኞችን የሚወድበትን ምክንያት ተመልክተናል። በምንም ዓይነት አገልግሎት ውስጥ ይሁን፥ የምታገለግላቸውን/የምታገለግያቸውን ነፍሳት የምትወድበትን/የምትወጂበትን ምክንያት ዘርዝር/ዘርዝሪ።

2. ፍቅር የሌለበት አገልግሎት ምን ዓይነት ይመስልሃል/ይመስልሻል?

3. የእውነተኛ ፍቅርን ባሕሪ ዘርዝረህ/ዘርዝረሽ ጻፊ። (1 ቆሮ. 13፥4-7)

4. ጳውሎስ ዕብ. 13፥2-3 ላይ *"...ከእነርሱ ጋር አብራ ችሁ እንደ ታሰራችሁ ያህል ሆናችሁ እስረኞችን አስታውሱ፤ እናንተም እንደ እነርሱ መከራ የምት ቀበሉ ያህል ሆናችሁ መከራ የሚቀበሉትን አስቡ"* ይላል። በዚህ ዓመት ውስጥ ይህንን ትዕዛዝ በተግባር ያዋልክባቸውን/ያዋልሽበትን ጊዜና ሁኔታ ጻፍ/ጻፊ።

5. ከላይ ያየነውን ትዕዛዝ በተግባር ላይ እንዳላዋልከው/እንዳላዋልሽው ከተሰማህ/ከተሰማሽ፥ ወደፊት ለመውሰድ የወሰንከው/የወሰንሽው እርምጃ ምንድነው?



*የትምሕርቱ አዘጋጅ*
*መለሰ ወጉ*

# ስንቅና ትጥቅ

**በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።**

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

**የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ**